# የዲያብሎስን ሥራ ያፈርስ ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ።

፩ኛ ዮሐ ፫፥፰

የዛሬ ሁለት ሺህ አራት ዓመት በምድራችን ድንቅ ነገር ተደረገ። እግዚአብሔር የሰው ልጅ በኃጢአት ከወደቀበት ጊዜ ጀምሮ በብዙ መንገድ በነቢያት አንደበት ሲያናግር የነበረውን ተስፋ ለመፈጸም ወደ ምድር መጣ። በንጽሐ ሥጋ በንጽሐ ነፍስ ፍጽምት ከሆነች ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን፣ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ ያለዘርዐ ብእሲ ተጸንሶ በፍጹም ድንግልና ተወለደ። በዚህም የማይወሰነው ተወሰነ፤ የማይታየው ታየ፤ የማይዳሰሰው ተዳሰሰ። የሰማይ መላእክትና እረኞች በሕልውና ከሰማይ አባቱ ሳይለይ ድንግል እናቱ የታቀፈችውን ጌታ አመሰገኑት። ሰብአ ሰገል ሰገዱለት እጅ መንሻም አቀረቡለት።

ለዘላለም በልዕልና የነበረ እግዚአብሔር የሥጋን ባሕርይ /መወለድ፣ መብላት፣ መጠጣት፣ መተኛት፣ መድከም. . . / ገንዘቡ አድርጎ በሥጋ ለመገለጥ /ለመወለድ/ ምን አተጋው? ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ በመልእክቱ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ዐቢይ ዓላማ «የዲያብሎስን ሥራ ያፈርስ ዘንድ፤» መሆኑን ገልጧል። የዲያቢሎስ ሥራ ምንድነው?

## ***<u>፩. ክህደት</u>***

በዓለም መላእክት ከልቡናው አስቦና አመንጭቶ የእግዚአብሔርን አምላክነት በመካድ «እኔ ፈጠርኳችሁ» በማለት ክህደትን ወደ ዓለም ያመጣ እርሱ ዲያብሎስ ነው። ከዚያን ወዲህም የሰው ልጆች በነፍስ በሥጋ ተሰብስበው በአንድ ልብ እውነተኛውን አምላክ ልዑል እግዚአብሔርን እንዳያመልኩ የሚያስት በዓለም የክህደትን እንክርዳድ የዘራው ይኼው ዲያብሎስ ነው። /ማቴ ፲፫፥፴፮-፵/

ክብርና ምሥጋና ለጌታችን ይሁንና ፍጹም እምነትን ሰጥቶን ዲያብሎስ ወደ ዓለም ያመጣውን ክህደት አራቀልን። አስቀድሞ *« . . . አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ፣ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ። የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ፤ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ፤ መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ። በትእዛዜም አስኬዳችኋለሁ . . .»* ብሎ ባናገረው መሠረት እንደ ድንጋይ የጠናብንን ክህደት አርቆ ወደ እርሱ የምንቀርብበት እምነት ሰጠን። /ሕዝ ፴፮፥፳፮-፴፪/

## ***<u>፪. ትዕቢት</u>***

ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ፣ ያልሆኑትን፣ ያልሠሩትን እንደሆኑና እንደሠሩ አድርጎ መናገር ነው። ይህ በመጀመሪያ ከዲያብሎስ የተገኘ ክፉ ጠባይ ነው። ዲያብሎስ ፍጡር ሲሆን በትዕቢት ተነሣስቶ በመላእክት መካከል መለያየትን ዘራ። ይህን ትዕቢቱን ነቢዩ ኢሳይያስ «አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ? አሕዛብንም ያዋረድህ አንተ ሆይ እንዴት እስከ ምድር ድረስ ተቆረጥህ? አንተም በልብህ ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፣ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ። በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ። ከደመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ። በልዑልም እመስላለሁ አልህ። ነገር ግን ወደ ሲዖል ወደ ጉድጓድም ጥልቅ ትወርዳለህ» በማለት ከነውጤቱ ተናግሯል። /ኢሳ ፲፬፥፲፪-፲፫/

ምንም እንኳን ዲያብሎስ የወደቀበትን ትዕቢት በሰው ልቡና ቢዘራም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትኅትና ትዕቢትን አራቀልን። ቅዱሱና ዘላለማዊው አምላክ ራሱን በፈቃዱ ዝቅ አድርጎ ሰው መሆኑ፣ ዝቅ ብሎ የደቀመዛሙርቱን እግር ማጠቡ ትዕቢትን ያፈረሰባቸው ትኅትናዎቹ ናቸው።/ ዮሐ ፲፫፥፬-፲፯/ በመዋዕለ ስብከቱም «ከእኔም ተማሩ፣ እኔ የዋሕ በልቤም ትሑት ነኝና ለነፍሳችሁ እረፍት ታገኛላችሁ» በማለት መምህረ ትኅትና መሆኑን አስተምሮናል። /ማቴ ፲፩፥፳፱/

## ***<u>፫. ሐሰት</u>***

ዲያብሎስ ወተቱን አጥቁሮ፣ ጣፋጩን አምርሮ ማቅረብ ሥራው ነው። አዳምና ሔዋን ሕገ እግዚአብሔርን እንዲሽሩ ከገነት እንዲወጡ ያደረገው በሐሰት ምክሩ ነው። « . . . ሞትን አትሞቱም ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ ነው እንጂ» እንዲል። /ዘፍ ፫፥፴፭/

ዲያብሎስ በሐሰት አዳምና ሔዋንን ቢያስታቸውም እውነት የሆነ ጌታችን በሥጋ ተገልጦ እውነት ወንጌልን ሰበከልን /ዮሐ ፲፬፥፯/ በዚህም እውነትን ዐወቅን። «እውነትን የምታውቁ ስለሆናችሁ ውሸትም ሁሉ ከእውነት እንዳልሆነ ስለምታውቁ እንጂ እውነትን ስለማታውቁ አልጻፍላችሁም» /ዮሐ ፪፥፳፩/ ጌታችን ሐሰትን አርቆ እውነትን ሊያጸናልን እንደመጣ «እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ፥ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ። ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል» ብሎ ለጲላጦስ ባስረዳው መሠረት አስተምሮናል። /ዮሐ ፲፰፥፴፯/

## ፬. ነፍሰ ገዳይነት

አዳም ሲፈጠርም ሆነ ልጆቹ ሲወለዱ ሞት ምን እንደሆነ አያውቁም ነበር። ዲያብሎስ በክህደቱና በትዕቢቱ ያጣትን ገነት አዳም በማግኘቱ ክፉኛ ቀናበት። በሐሰት ምክሩ የተሰጠችውን ርስት ገነትን እንዲያጣ አደረገ። በዚህም ሳያበቃ የአዳም ልጆች እንዲተላለቁ ሞትን ለቃየል አስተማረ። ቃየል መሥዋዕቱን እግዚአብሔር እንዳልተቀበለለት ሲያውቅ በወንድሙ ላይ ቀና። ቂሙን በልቡናው ይዞ ወንድሙ አቤልን ወደሜዳ ሄደን እንጫወት አለው። በጨዋታ ላይ እንዳሉ ሰይጣን በጥቁር አሞራ መልክ ተገልጦ ሌላኛውን አሞራ ራስ ራሱን (እንደሚናተፉ ዶሮች) መትቶ ገደለው። ይህን ያየ ቃየል ቂሙ ጥላቻው አድጐ ስለነበር አቤልን በድንጋይ ወግሮ ገደለው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ዲያብሎስ ባስተማረው ነፍሰ ገዳይነት የአዳም ልጆች ሲተላለቁ ይኖራሉ።

ዲያብሎስ ነፍሰ ገዳይነትን ቢያስተምርም ክርስቶስ ግን ነፍስን መስጠትን (ስለሌላው መሞትን) አስተማረ። በመስቀል ተሰቅሎ ስለሌሎች የሚሞትበትን የክርስትናን ሕይወት ሰጠን። ለዚህ ነው ሰማዕታት በሃይማኖት ምክንያት መከራን ለሚያጸኑባቸው፣ ለሚወግሯቸው ይቅርታን ይለምኑ የነበረው። /የሐዋ ሥራ ፯፥፰/

## ፭. ማሰናከል

ዲያብሎስ ምንጊዜም ቢሆን የሰው ልጆችን ድኅነት አይሻም። በመሆኑም የሚስቱበትን የሚሰናከሉበትን ምክንያት ከመፍጠር ወደ ኋላ አይልም። ይህን የመሰናከል መረቡን የሚዘረጋው በተለያዩ መንገዶች ነው። እሥራኤል በእግዚአብሔር ረድኤት ከግብጽ የባርነት ኑሮ ሲወጡ ተስፋ ወደሚያደርጉት ምድረ ርስት እንዳይገቡ ብዙ ጊዜ አሰናክሏቸዋል። ከነዚህም አንዱ በባሶር ልጅ በበለዓም አድሮ ለባላቅ የመከረው ምክር ነው። ባላቅ እሥራኤልን እንዲረግምለት በለዓምን ጠራው። እግዚአብሔር የባረከውን መርገም እንደማይቻለው ያወቀው በለዓም በዓመፅ ሥራው ከባላቅ የሚያገኘው ገንዘብ እንዳያመልጠው «አንተ የምትሻው የእሥራኤልን መጥፋት ከሆነ ባልረግምም ከወገኖችህ ቆነጃጅቱን መርጠህ አልብሰህ፣ ቀብተህ መስዋዕተ ጣዖትን አስይዘህ ወደ እሥራኤል ላካቸው። እሥራኤል ፈቃዳችንን ፈጽሙልን ይሏቸዋል። በዚህን ጊዜ ቆነጃጅቱ ፈቃዳችሁን እንድንፈጽም ፈቃዳችንን ፈጽሙልን መሥዋዕተ ጣዖቱን ብሉልን ለ«አማልክቶቻችን» ስገዱ፣ ይበሏቸው። በዚህ እግዚአብሔር እሥራኤልን ያጠፋልሃል ሲል እሥራኤል የሚሰናከሉበትን ምክር አቀረበ። በዚህ ምክሩ ወደ ምድረ ርስት ይጓዙ ከነበሩ እሥራኤላውያን መካከል ሃያ አራት ሺህ ያህሉ አለቁ። /ዘኁ ፳፬፣ ፳፭፥፩-፱/

ቅዱስ ዳዊት «መሥገርትሰ ተቀጥቀጠት ወንሕነሰ ድኅነ፣ ወጥመድ ተሰበረ እኛም ዳን (አመለጥን)» ብሎ እንደተናገረው ዲያብሎስ ያሰናከልበት የነበረው ወጥመድ በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ጥምቀትና ስቅለት ተሰበረ። /መዝ ፩፻፳፫፥፯/። አዳምን በዕፀ በለስ ቢያሰናከለው ጌታችን ወደ መንግሥቱ የምንገባበትን ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ሰጠን። ቀድሞ በኃጢአት ጨለማ ተይዘን የጽድቅና የኩነኔን መንገድ ባለማወቅ እንሰናከል የነበርን ዛሬ ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን ሆኖን ከመሰናከል አወጣን። /ዮሐ ፰፥፲፪፣ ፩ኛ ዮሐ ፩፥፭-፯/

በነዚህም የዲያብሎስ ሥራዎች ፋንታ ሰውን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡ፣ ፈቃደ ነፍሱን የሚያለመልሙ ያጣውን መንግሥት ለመውረስ የሚያስችሉ አምላካዊ ስጦታዎችን እንዲሁ (በጸጋ) በቸርነቱ ሰጠን። በጌታችን መወለድ ያገኘናቸው ሥጦታዎች፡-

## ሀ. ልጅነት

በጥንተ ተፈጥሮ እግዚአብሔር አባት፣ አዳም ልጅ ነበር። እግዚአብሔርን አልሰማ፣ ትዕዛዙን አልጠብቅ ብሎ ራሱን በፈቃዱ ካሠማራ በኋላ ግን ይህን ክብር አጣ። ልጅ የነበረው ባሪያ ሆነ። በባሪያ ሥርዓትም የሚለፋ ክብር የሌለው ሆነ። /ዘፍ ፫፥፲፰/

ባርነቱ የከበዳቸው አበው ጮኹ መሥዋዕት አቀረቡ። በመሆኑም በጌታችን ልደት ርቃን የነበረችው ልጅነት ቀረበችን ተሰጠችንም። ቅዱስ ዮሐንስም የዚህን እውነታ «ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው» ሲል ገልጦታል። /ዮሐ ፩፥፲፪/ ይህም የሆነው በቸርነቱ ነው «የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ» እንዳለ። /ዮሐ ፫፥፩/

## ለ ነፃነት

ልጅነት የተሰጠን ዕዳ ያለበትን ልጅነት አይደለም። በአዳም ምክንያት ወደ ዓለም ከገባው ርግማን ፍጹም አርነት አውጥቶን ነው። «በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን። እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ። እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ።» /ገላ ፩፥፩/ ይህንን ነጻነትም ዳግም እንዳናጣ «አርነት ወጥታችሁ እንደ እግዚአብሔር ባርያዎች ሁኑ እንጂ ያ አርነት ለክፋት መሸፈኛ እንዲሆን አታድርጉ» ተብሏል። / ፩ኛ ጴጥ ፪፥፲፮/

## ሐ. ፍቅር

በኃጢአት ምክንያት በሰውና በእግዚአብሔር፣ በሰውና በመላእክት፣ በነፍስና በሥጋ፣ በሰማይና ምድር መካከል ጥል ሆነ። በዚህም ፍቅር ከእኛ ራቀ። ፍቅር የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቡ ነው። በመሆኑም አንድ ሰው ፍቅር የሚኖረው ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት ሲኖረው ነው። «እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል» እንደተባለው። /፩ኛ ዮሐ ፬፥፲፯።

የዚህ እውነታ በግብር የተገለጠው ጌታችን የሰውን ሥጋ መዋሐድ ሳይጠየፍ ሰው ሆኖ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ጥሩ መዓዛ እንኳ በሌላት በከብቶች በረት በተወለደባት ሌሊት ነው። በዚህ (በልደቱ) የጀመረውን ፍቅር ፍጹምነቱን ለዓለም ያሳወቀው በመስቀል ተሰቅሎ ነው። «ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም» /ዮሐ ፲፭፥፲፫/

## መ. ሰላም

ከእግዚአብሔር ጋር የተጣላ ሰላም የለውም። ምክንያቱም የሰላሙ ባለቤት እግዚአብሔር ርቆታልና። ጌታችን ተወልዶ በጨርቅ ተጠቅልሎ በከብቶች ግርግም በተኛባት ሌሊት መላእክት «ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጐ ፈቃድ» ብለው ሰላምን አወጁ። /ሉቃ ፪፥፲፬/

ይህ ሰላም በሸንገላ የተመላ፣ ምድራዊ ኃይል አይደለም። «ሰላምን እተውላችኋለሁ። ሰላሜን እሰጣችኋለሁ። እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም» በማለት ጌታችን እንዳስተማረው የማንቀማውን ሰላም አጐናጽፎናል። /ዮሐ ፲፬፥፳፯/

## ሠ. ዘለዓለማዊ ሕይወት

አበው ሲናገሩ «የነፍስ ሞቷ ከእግዚአብሔር መለየቷ» ነው ይላሉ። በመጽሐፍ ቅዱስም ነፍስና ሥጋቸው ሳይለያዩ በኃጢአታቸው ከእግዚአብሔር በመለየታቸው «ሞቱ፣ ሙታን» የተባሉ አሉ። ለምሳሌ የጠፋው ልጅ /ሉቃ ፲፭፥፳፬/። ዛፍ (ቅርንጫፍ) ልምላሜ ኖሮት ፍሬ ሊያፈራ የሚቻለው ከግንዱ ጋር አንድነት ሲኖረው ነው። ከተቆረጠ ግን እንኳን ፍሬ ማፍራት ቀርቶ ዕጣ ፈንታው መማገድ ነው። /ዮሐ ፲፭፥፩-፯/ እንደዚሁም ሁሉ አዳምና ሔዋን ሕግን በመተላለፋቸው ከሕይወት ግንዳቸው ከልዑል እግዚአብሔር ከነልጆቻቸው ተለዩ። ከእሳቱ ከሲዖል ተጣሉ።

ጌታ ተወልዶ ሕይወቱን ሰጠን። ሕይወት ሆነን። ሞት እንዳያገኘንም «ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳን ሕያው ይሆናል» ብሎ አስተማረን። /ዮሐ ፲፩፥፳፭/ በመሆኑም በርሱ የባሕርይ አምላክነት አምነን የተገኘን ሁላችን እምነታችንን በመልካም *ሥራ* ገልጠን ከኖርን ከኃጢአት ከተጠበቅን ሕይወት አለን። /፩ኛ ዮሐ ፪፥፮፤ ፭፥፲፪፤ዮሐ ፫፥፴፮/

ዛሬ በአምላካችን ቸርነት ጽድቃችንን የመርገም ጨርቅ አድርገው የነበሩ የዲያብሎስ *ሥራዎች* ተወግደዋል። ለመሆኑ ከነዚህ የጠላት *ሥራዎች* የተጠበቅን ስንቶቻችን ነን? ቅዱስ ዮሐንስ «ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፤ ዘሩ በእርሱ ይኖራልና ከእግዚአብሔር ተወልዶአልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም» ብሎ እንዳስተማረን በአምላካችን ቸርነት ልጆቹ የሆንን ሁሉ ጌታችን በግብር ያሳየንን *ሥራዎች* ያለመታከት የምንመራባቸውና የምንሠራቸው ከሆነ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችን ይገለጣል። ሌሎችም ከዲያብሎስ *ሥራ* ተጠብቀን ፈቃደ እግዚአብሔርን መፈጸማችንን ዐይተው ወደ እግዚአብሔር ይቀርባሉ። /፩ኛ ዮሐ ፫፥፱/

በስሙ አምነን ተጠምቀን ልጅነትን ካገኘን በኋላ በፍጹም ልብ ከማመን የምንጠራጠር፣ እውነትን ከመናገር ሐሰትን የምንወድ፣ ትኅትና የሌለን ትዕቢተኞች፣ ቅድስናችንን ጥለን የምንዋረድ ከሆነ እግዚአብሔርን አላወቅነውም። /፩ኛ ዮሐ ፫፥፮/ በመሆኑም እግዚአብሔር በሰጠን ዘመን ሁሉ እንደ ቅዱሳን እርሱ የሚደሰትበትን፣ ወደእርሱ የሚያቀርበንን መልካም *ሥራ* በመ*ሥራ*ት እንኑር። ቅዱስ ዮሐንስ «በእርሱ እንዳለን በዚህ እናውቃለን። በእርሱ እኖራለሁ የሚል እርሱ እንደተመላለሰ ራሱ ደግሞ ሊመለስ ይገባዋል» ብሎ እንደመከለረን እግዚአብሔርን አጋዥ አድርገን ከላይ የዘረዘርናቸውንና ሌሎችንም የዲያብሎስ *ሥራዎች* የምናፈርስ ከሆነ በእርሱ በክርስቶስ አምነናል። /፩ኛ ዮሐ ፪፥፮/

ስለዚህ ዳግም በባርነት ቀንበር ተይዘን በማይፈጸሙ ዘመናት በገሃነመ እሳት እንዳንማቅቅ ከዲያብሎስ *ሥራ* በንስሐ፣ በ*ሥጋ* ወደሙ እንለይ። የዲያብሎስን *ሥራ* ሊያነግሡ ከሚሯሯጡ የግብር ልጆቹ እንጠበቅ። ከበዓለ ልደቱ በረከት ያሳትፈን። አሜን።

*ምንጭ፡- ሐመር መጽሔት ታኅሣሥ/ጥር 1991 ዓ.ም. ዕትም*